
# ከማሁ ፍቅረ ቢፅ



# መቅድም!

‹‹ስስ ግጥም ካነሳህ አይቀር ቀለሙ ከታጣህ ‹መቁ›ን አሶግደህ ‹ጥልቁ›ን እየተካህ ሳድሱን አዋደህ አንተ ቀለም ቁጠር እኔ ግን እስከዛው ብችል ግጥም ልገጠም፡፡››

‹‹ሀሳቡም ተበትኖ አንዳንዴ ግጥም ሙዝዝ ካለብህ ራስህን ሰብስብ አድርገህ መክሊትህ እንዲሆን ደግመህ ደጋግመህ ተሟዘዝበት፡፡››

‹‹አንድ ሐይማኖተኛ እምነት እንዲኖርህ ራስህን ጣል ይልሀል፡፡ በርግጥ ማንነትህን ማን ስሆነው ኃያል አምላክህ ስጥ ማለቱ እንጂ አፈር የሆነውን ሰውነትህን ጥለህ ባት ማለቱ አይረደስም፡፡ ነገር ግን በግጥሙ ዓለም እሱ እስካሳሰከረህ ሌሳውን ተረድቶ ከራስ ሰውነት ስመሆን አስትንፋሳዊ የሆነውንም ይሁን ስጋዊ አካልህን ጥንቅቅ አድርገህ በቅጡ ሰብስብ፡፡››

‹‹በምድር ሳይ ከታደሉ ጥቂት ሰዎች ከነሱም በትንሽ ካልሆነ በስተቀር የሚሰማቸው የስም እንጂ ሁሉም ግኡዝ የተባለ ፍጥረት ለሰው ልጅ በተለየ መልኩ ንግርቱን ያበስረዋል፡፡ ግን ብንችል አብሪተኞች ካልሆንን የስሜት ህዋሶቻችንን ተጠቅመን የራስ ቀሳችንን ቀጥቅጠን እየኮረኮርን እናዳምጣቸው፡፡

‹‹ሰው እንጂ ወንዝ ሰው አይዘልም ግን ከተሸገርን ዕምድረ-ገነት ወይም መንግስተ ሰማይ አለና ጎርፍ እስኪጎል በተስፋ እና በትዕግስት ካለንበት እንቆይ፡፡››

ከገጣሚው

✍ የቀድሞ ሥራዎች

1. **ሐማንዳብ** በ2013ዓ.ም ልብወለድ
2. **እኛ የጭንቅ ዘመናቶች** በ2014ዓ.ም ኢ.ልብወለድ

በአብነት ሲራጅ

# *መግቢያ!*

በመጀመሪያ ከዚህ ሥራ በፊት ማለትም ‹‹እኛ የጭንቅ ዘመናት›› እና ‹‹ሐማንዳብ›› በተሰኘው ድረሰት ሳይ እስካሁኗ ጊዜ ከጎኔ ስነበራችሁ ዘመድ ወዳጆቼ በተለይ ታናሽ ወንድሜ ግን ታላቅ ሰው እንዲሁም ውዱ አጎቴ በርግጥ ለከፈላችሁልኝ ውለታ የምከፍለው ገንዘቡም ሆነ አቅሙም ቢሆን የለኝም እና እናንተም ከፈጣሪ በላይ የምትሹት ከሱም በላይ ስጦታ ሳይኖር የለም እና አምላክ ከምመኝላችሁ በላይ አብዝቶ እና መርቆ ይስጥልኝ።

ግጥም ካለፉት ዘመናት እስካሁኑ እንደምንረዳው ከሆነ የሰው ልጅ ሲከፋ እና ሲደሰት በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊው ህይወት ውስጥ ቃላት መርጦ ከሀረግ እያዋደደ በስንኝ ራሱን እያናኘ በቀመር የውስጡን የሚሰድርበት ሌላውን ካለበት ነቅንቆ የሚያነቃበት የሰውነት መቃኛ የጥበቡ መናግርት ዋሸንት ነው።

ግጥም ላይ ጎበዝ ባልሆንም ስሜት ሰጥቶ መቡከሪያ ቢሆነኝ አንብቢያቸዋለሁ፤ በመጠኑም ቢሆን ተረድቻቸዋለሁ ካልኳቸው ግላዊ የገሀዱ ዓለም አረዳድ የራሴን ትንሽ እና ቁንፅል ሥራ ከናንተው በዚህ መልኩ ቢደርስ ብዬ ወደድኩ።

በ2014ዓ.ም

በ2021G.C

ፍቅረ ቢፁ ቢያድለኝ በርግጥም አናንተ ግጥሙን ሰድሩ እኔ ግን ትንሽ ግጥም ሞካክሬ ልከትብ።

# ክፍት ሲልህ

የቀን ንቃቃት በህይወት በርትቶ፣
የውስጥ ድባት በማጥ ደም ደክርቶ፣
ተስፋ እልም ጭልም ብሎ፣
ይኸው ነው ሰው ስልም ገሎ፣

በግግር የነፍስ በረዶ፣
ስብር አቅለቢስ ተጋርዶ፣
ክፍት ሲልህ አግምሞ፣
ያሳቅላል ከዝናብ አስጋሞ፣

በእትቱ ብርድ እያስሸከሸከ፣
በብዕር ወረንጦ እያሸከከ፣
ሳይትርፍ አቋምሮ እያንቋጨጨ፣
ያካፋል ክርም እያንቀራጨጨ፣

በቋጥኝ ክብ ጭቃ አስምጦ፣
በሀፅያት ረብጣ ወገቡን አግብጦ፣
ልቦናን አንኩቶ በድንጋይ የቀጣ፣
ደስታ ክፋት ነው በክፋት የመጣ፡፡



## ✍ ሰንደቅ ዓላማ

ለዓለም ቃል-ኪዳን ጥበቡ ብርሃኑ ቃል የደገሰሽ፤
ሳይተው አክብሮ በልጁ ምሎልሽ ቃሉን ያበሰረሽ፤
ሰማይ ሳይከልለው በማንቢያ ደፍ መቅኖ የታጠቃት፤
ሰንደቅስ ምን አሳት ለእጅ መርቅ መዳብ ከነሳት፤

የስንቱ ደም ፈሶ አቅል ነስቶ አጥንቱ ረግፎ፤
በርሃብ ንዳድ በውሃ ጥማት አንጀቱን ገርፎ፤
በፍቅር እጦት መዐበል ሁሉም ስጋው አልቆ፤
ሳንቺ ሲል ስንቱ ይሆን ከጠላት ያልቆመ ተናንቆ፤

አገኝ እንደሁ ብሎ በሰው ሀገር ቢበር፤
በባህር ወጀቡ አዝኖ ሲናፍቀው የሰፈሩ መንደር፤
ወገንም አይደርሰው በእናትም ግኖ፤
አንቺ እኮነሽ ያኔ የልቡ ተስፋ የዐይኖቹ
ወጋገን የእጁ ሳይ መኖ፤

ጠላት አሻፍሮት በጉራ ሲሸልል ሲያቅራራ፤
ጦር አዝምቶ ድንበር ቀርጦ ሲኩራራ፤
ሳይቆይበት ብርክ ይዞት ሲጎብጥ፤
ስንቱ ያልገባ ይወጣ ነበር ከሰርጥ፡፡



# ጥሪ ከሞላበት

ወንድሜ ሲልህ እስትንፋስ አጥሮት፤
ከአጠገቡ ስትርቅ ዘመድ አንቅሮት፤
ስጋውን ሲመኝ ውስጥ ራስስ ብልቦት፤
ዛሬ እንኳን ይረፍ ከቁም ሙት ገሳግሎት፤

ዐይኖቹ ማትረው ከአሸኑ መሐል አንተን ሲፈልጉ፤
ብታድነው መስሎት ከናፍሮቹ ታች ሳይ ለጥሪ ሲሳጉ፤
ተስፋ የተሞላው ማንነቱ በሞት ጥላ ስር ደብቦ፤
ለካስ አልሞት ነበር የመጣው መረቡን አርግቦ፤

ቀን ነግቶ በመሸ ቁጥር ሁሌ ሴጣ አንፈራጦ፤
ከመድረሱ ለፍየል የዛፍ ባላ ቅጠል አስልጦ፤
አሁን ምን ሲያመጣ ወግድ ወጊዷ ማለቱ፤
ያኔ ነበር እንጂ ጨለማ አማልዶ ማንጋቱ፤

ሄዳ ሳትመለስ ያዳም ስስት ህይወት፤
በርጉም በቅሎ አንሳ ሁሌ እየጋለቢት፤
አትሄድ ቢመስላቸው ቀብጠው ያፋነኗት፤
ስንቱ ከርካብ ቀረ በቅጡ ፍኖ ሳይጋልባት፤

ሳይመስል እንደሆን ጤፉ በአፍ ተቆልቶ፤
በወላፈን እሳት የባቄላ አገዳ አንኩቶ፤
እሸት አይሉት ነገር አደቁሰው በልተው፤
ተወው ጥሪ ከሞላበት አሞራ ይፈሰው፡፡



## ✍ ቅንቅን

*መንደር በሀር ጠቃጠቆ በውሃ ተሞልታ፤*
*የቃልሽክም ከንትብ ድግድግ ንቅ አቃብታ፤*
*በተገለበጠ ዐይን በንክ ጆሮ አዕምሮ ዝጋ፤*
*በሰባ ዕድሜ የከረፋ ከንቱ ጦር አደግድጋ፤*

*በሎጂክሰ ነፍስ ብከት ትንቢት ተበድሎ፤*
*ሰውነት በቁጫጭ ቁንጫ ተመንድሎ፤*
*ዝግን መሳይ በትዕቢት መርዝ ተከሽኖ፤*
*አባት ነኝ ይለኛል በመፍዙዝ ነፈዝ ገኖ፤*

*በማዳን ፈንታ ሴሳውን ደም እያራጨ፤*
*በማዋደድ ፈና ግራ ከቀኝ ነርቶ እያጋጨ፤*
*ብርሃን አስክዶ ጭለማ ጭን እያዳከረ፤*
*ንፁ ነኝ ይለኛል ገዳይ ክር እያካረረ፤*

*በክህደት መንደር ምላስ እየጎለጎለ፤*
*በጓዳ እልፍ አባይ ሰይጣን እያባበለ፤*
*ፍጡር በፈጣሪው ስም ታርጋ እየለጠፈ፤*
*አለሁልህ ይላል ወሽክቶ ነብሴን እየሸጠ።።*

❖ ♥ ♦



# ✍ የጨለመ ጉዞ

*ባቀበት ተራራ ሀሳብ ተደግሶ፤*
*በሰው ተራ ህይወት ተደርምሶ፤*
*ከህሌና ኮርቻ ቅስም ተሰንጥቆ፤*
*ምን ሲበጅ ደንያ እንቆቆ አጭቆ ፤*

*ልጓሙ አልጋሚ እርካቡ ስንቅር፤*
*የአፍንጫ ትንኝ የአንደበት ቅርቃር፤*
*ሲያመሽ አጨግጎ እያጨለመ ንጋት፤*
*ድሮስ መች አልቆ የአቀበት ፍጋት፤*

*ድን ልብ እልም ስልም እያለ፤*
*ዐይን ክርትት ስቅ ስቅል ሲል፤*
*ጎዳናው እግር በጨጭ እያዛለ፤*
*መች ሲያፋታ ከጊዜ እያማለለ፡፡*



# ✍ተረት

በምሳሌ ህይወት ምጣት ቀኖችን ሲፈጁ፤
የሴትን ጭጋግ ከቀን ጠምቀው ሲያራጁ፤
በነፈሰበት ነፈዝ ቃል በቃና ዜማ እያዜሙ፤
ማጭዶችም ከፉ ቦይ ለቦይ መም እያመሙ፤

በስራስር ብጣሽ ገመድ አየር እየሰፉ፤
በአውሳሳ ሜዳ ቆዳ ቁርበት እያሰፉ፤
በሰንሰለት ችካል ሴንጢ እየሰነቀሩ፤
ያስጥል ያስከንፋል ገመድ ካከረሩት፤

በኒኮቲን እርካብ አርሰኒክ ሲጋልብ፤
በቅጠል ፂም ሰንጋ ቀንድ ሲቀልብ፤
በቅል ናሳ ዝሎ ዞርሮ አፅምሮ ሲንካካ፤
ያኔማ አያዋጣም ተረት አባብሎ እንካ፡፡



## ፍቅር

ኃያሉ ማንነት በፍቅር ታውሮ፤
አንደበት በስቃይ ሉጓም ታስሮ፤
ዐይኔ ካይኖችሽ በሰመመን ወስልቶ፤
ልቤ ባዳ ሆነ ከመሳው ሰውነት ተጣልቶ፤

በወሳፈኑ ውስጤ እያረረ ቀን በቀን ተወልዶ፤
በጎመራው እሸት እንቡጥ ካገዳው ተጋምዶ፤
ያረገዘው ግርግር በእሳት ግሞ፤
መች ይሆን ያንቺ ቀን ከእኔ አቅምሞ፤

በአንጎል ቅሉ ብጥብጥ አሳምኖ፤
ሳይዘለቅበት ነገር በፍቅር መንኖ፤
ልብ ሳይገባ ከመቃብር ፈንቅሎ፤
እንዴት ሊዘለቅ ራሱን ቆርጦ ቀጥሎ፤

መውደድ በደም ስር ታልቦ፤
ስጋ በነፍስ አቅል ተገልቦ፤
ድንገት ልብ በልብ ተማርኮ፤
እስከመቼ ይሆን በፍቅር አስታኮ፤

አንጀት ከጅማት ገልብጦ፤

የአፍሳ አጥንት አግጦ፤

አይድንበት ውበት አቆሳቆሶ፤

እስከመቼ ድረስ ከራስ ተፈራርሶ፤

በሀሳብ አናኝቶ ከቤት ደጅ ፈልቅቆ፤

ሴቱ በእንቅልፍ ሳያስተኛ ሰብቆ፤

ቃል በምድር በሰማይ ተስፑ፤


ለማን ይሆን ፍቅሬ የሚቀረው ግፎ፤

ብሸሸው ሳይተወኝ በምናብ አስሎ፤

በውሎ ትዝታ ጭንቅን ቆልሎ፤

ዛሬማ ካልጠፋሽ መንገዱ ሲሆንልሽ ድልበድል፤

ልቤማን ይኸው ያሰረውን ውል ሳይፈታ ወዶሻል።



## ✍ እኛ እኮ ነን

*ጠሳት በመትረይስ ሴት ተቀን ሲያናፋ፣*
*ንብስያ ተጨንቃ በደም ስጋ ስታሳፋ፣*
*ሀገር በጥምቅ አባራ ተካሳ፣*
*እኛኮ ነን የሆናት ጥሳ ና ከለሳ፣*

*በመድሃኒት መርዝ በትነው፣*
*በቅርጫት ሸቀጥ መድበው፣*
*ሆድ ሲሞሉ ባንዳ አግዘው፣*
*እኛኮ ነን አዳምን ያዳነው፣*

*ባዳ ሲውተረተር ኢትዮጵያን ሲያጠፋ፣*
*እንደ ሸንኮራ አገዳ መጥምጦ ሲተፋ፣*
*እባብ ሆኖ ሲናደፍ ሲመጣ ነዶ፣*
*ያኔ ባንድነት መልሰናል ዘንዶ፣*

*በድቅድቅ የባህር ጭለማ፣*
*ወዝ በሌለው የሰውነት ገልማ፣*
*ወገን መቅኖ አጥቶ ሲንገላታ፣*
*እኛማ ሆነናል የእውቀት ገበታ፡፡*



## ✍ አይችልም አንጀቴ!

*በነፈሰ ነገር አንቀልባ ወርቅ አዝሎ፣*
*በማግኘት አቀበት አንደበት አንጋሎ፣*
*በእንቁላል አስኳል መንደሩን ከትቦ፣*
*እኔ መች አልተኛ አልኩ አልጋ ረግቦ፣*

*በሌለ ጎንትለህ ብትቀደኝ፣*
*በመበዓህ ጭንቅ ብታሳጣኝ፣*
*ስል ካራህን ብታስረው ባንጀቴ፣*
*እኔማ ባንተ አይጨክን አንጀቴ፣*

*መቅኖ ኩስም ድቅቅ ስትል፣*
*አጥንትህ ጋራ ተራ ስትዝል፣*
*ሰው በመሆን ክፋት ሲዘንብብህ፣*
*እኔን አያስችለኝ ሌላም በመሆንህ።*




# ምሳስ

እውነትን አንቅሮ እየተፋ፣
ክህደት አብልጦ እየሰፋ፣
ቀን በለሊት ወንፊት እያረሰ፣
እሱ ነው ፀፀትን ያልበሰ፣

ህሊናውን በጉያው ሸጦ፣
እሳቱን በምላሱ ልጦ፣
በእልፍኝ ገላህ ተስፈንጥሮ፣
ያጠፋኃል ሳይበጅህ ተሰንቅሮ፣

አመልን በላንቃው አንግቶ፣
በአጠና ምሰት አፈርን ተግቶ፣
ያውቀው ስህተትን ለጥፎ፣
እሱማ ነው ቁርጥ ክትፎ።



# ✍አዬ ጊዜ

*የእውቀትን በር በራሱ ሳይ ደርግሞ፧*
*ንቃትን በንጋት አህያ አልግሞ፧*
*ትውልድ አራንባ እና ቆቦ ረግዶ፧*
*ስንቱን አሳይቶናል ጊዜ ማልዶ፧*

*ቅጥፈት ስጋጅ ስባክ ሆኖ፧*
*እውነትን በሀሰት አመርቅኖ፧*
*ህሌና ሳይጠይቅ ምላስ ምጎ፧*
*ስንተ ስንቱን አሳዮን ገንፎ ልጎ፧*

*ድንቢጥን በዝሆን አስሎ፧*
*የስቡን ምሬት ሰማይ አሳክሎ፧*
*አንበሳን በዝንብ አርክሶ፧*
*ጊዜ ሁሉንም አሳዮ እሬት አስልሶ፧*

*በወርቅ መዳብን ጎልቶ፧*
*ሳይጠቅም ስጋጃ ጎትቶ፧*
*በቁስል እንባ አመርቅዞ፧*
*ማንስ ያሳዮው ጊዜን አርግዞ?!*



## *ታሞ ያልዳነ ሠው!!*

ህመም እንኳን አሞኝ

ለሰው አልናገር፤

ይባስ ይወጋጋኛል

ካሳር እና ምንቃር፤

ቢዳንልኝ መስሎኝ

ምርቃዜን ብሰጠው፤

በምርምር እጦት በኮፈኑ ብሶ

ልቤን አቆሰለው፤

አነጋገቶ ውሎ አመሻሽ ሳይደግም

ፊና በጥሪኝ እያሳፋ፤

በጠራራ ፀሐይ በምሽት ታውሮ

ቀን እያዋለው ሲያናፋ፤

ባልሰማው ጆሮ ባልኖረው አዱኛ

ውል ቋጥሮ እየገመደ፤

ስንቴ አስጨነቀኝ ህመም

እንኳን ታሞ እያነደደ፤

ኣልተወው ነገር ምኛት
ካሳብ ሰምሮ፧
ወኔዬም ኣስገምግሞ በጠጠር
ቋጥኝ ከምሮ፧
እርካቡን ብጫነው
እሬት ኣርግዞ፧
ደግሞ ያንሸራትታል
እንባ ና ጥርስ ታዝሎ ባዞ፧

በተፈጥሮ ሰማይ ኣየር
ንስር ካሞራ እያጣሳ፧
ነብር ንኳ ኣዝኖ ስጎሽ
ሆድ ቆርሶ እንዳያዳሳ፧
ኣበሳስቶ ሲያጋምድ መርፌ
ከክሩ እየተዋደቀ፧
መች ይሞቀው ነበር
ካንጀት የተሳቀቀ፧

ኣይጋልቡት ነገር የቆሙበት
ድንጋይ፧
ኣይበሩ ኣይዋኙት ልጓሙ
ተንጠልጣይ፧
በክህደት ስሊት ቀኑ ዳምኖ
በውነት ያልተረታ፧
እረ ይሄስ ከየት ይሆን
ምልጃው የተፈታ፧

ማረሻው እንደሁ ካልተዋደደ
ከሞፈሩ፧
ሳይበጅ ሆኖ ከበሮች ማነቆ
ማሰሩ፧
ሳይታረስ መሬትን ከሰማይ
አስታከው ካልጎመጎሙ፧
ታድያ ምን ያደርጋል ቀንበር
ጢጣ መሸከሙ

ውሃም በንፋሳት ህይወት
ዘርቶ ነፍስ ካሳዳነ፧
እሳትም ነዶ ንዶ ብርድ
ካሳሰከነ፧
ዋልታ ከፍርግርግ ካልያዘ
የምሰሶ መቆም፧
ድሮውንስ ምን ሲበጅ
የንፋሳት ዓለም፧

ባመሻሽ ባነጋጉ ወፎች እየዘመሩ

ካልነጋ ስሊቱ።

ፀሐይ ስቃ በቋር ከባሰ

ግስቱ።

ቃር አሳስችል ብሎ ምስር

ከገባ ከቤቱ።

ካበቃ ዓለሜ አልሞት

እንደሁ ልሙት።




# ✍ አያሻም!!

ተፈጥሮ በቅጠል ዛፍ ተንጠልጥሎ፤
የነብስያ መንጋ በስጋ አናት ተሰቅሎ፤
የማንነት ጥግ በዘር በድንበር ተቆርሶ፤
እንዴትስ ሲዘለቅ ከወንድም ተታኩሶ፤

በዕምድር ስቅል ግንት ሰማይ አርጎ፤
ጥብቅ ውትፍ ጭምድድ አድርጎ፤
ጃል ምረር ጠብቅ ግጠም አለኝሳ፤
በተኛ በፈጠጠ ዐይን አበሳ እያገሳ፤

ሲነጥቁት ቢመስለው ልቡ እየተሸበረ፤
ሲያስርቡት ቢታየው ውስጡ እያረረ፤
ዝግባ ሲያነፃ ነፃ አውጪ በራሱ ሥራስር፤
ምንለየው ወገኔን ያም ማገር ይም ሀገር፤

❖ ♥ ♦



# አይ! ስቃይ

ማልዶ ብርድና ውርጩ ከላይ እየወረደ፣
ንጋት ወቅቶ እብቅ ዓለሜን እያነደደ፣
በጋ በክረምት መባቻ ነዶ ፃሙን እየፈታ፣
ይሄስ ቅኔ ነው በመቀነት ቀሚስ የተረታ፣

ሆድን የመሰለ መርገምት ሁሉም ተሸክሞ፣
ሳትሞላ ቁጥር ሀሳብ በህይወቱ ከስሞ፣
በዘመነ ነጋሽ አንጋሽ ጭካኔን ቋጥሮ፣
ምንኛ ስንቃር ይሆን የመኖር ቋጠሮ፣

አይን እያስለመለመ ጅማት ሲያጭቅ፣
በካባ ጉልበት ተሰብሮ ቅስም ሲስቅ፣
እዕምሮ ቀልጦ በቅል ስብ አየሰባ፣
ምን ያለ ስቃይ ነው ሰው ለሰው የማይረባ፣

በእንግዳ እርካብ ባለጌ ተፈናጦ፣
ክፉን እያሳየ ማጀቱን ገልብጦ፣
የማያደርስ ቀን ባቀበት ዳገቱ ሆድን እየሰፋ፣
ለምን ይሆን ስቅል ስቃይ በአዳሜ የከፋ፣

ከዘመኑ ዕርክሰት በሸበተ ድንጋይ ብሶ፣
አሳለፈው ነገር ምንትፍ በንዋይ ታብሶ፣
በዙፋኑ መንበር ተጎልቶ ምን ሲሳይ ሲያመከን፣
ይሄማ መርገም ነው ለፍሬው መኖ ያልበተነ፣

ጊዜውን እየረገመ ካዋይ አሳዶ እየነጠቀ፣
ካልበሰሉ መዳፎች የጅ ጣት እየሰነጠቀ፣
ሹል ሾጣጣ አቀበት ተይዞ በወጣት፣
ነብስያን ወደዳት ተንፍጎ እየማጋት፣

ሰማይ ቀርቦ አፍ አየር እያረሰ፣
በአቧራ ሜዳ ጭስ እያስጨሰ፣
እሹሩሩ ቢሉት ንፋስን በአለት፣
መቼስ ሲመልሰው ሆድን በግለት።



# ✍ ሆድ ሲባባ

*በጠፋ ዐይን ሳይ ወይናግፍት ተደግልሎ፤*
*በማይሰማ ጆሮ የጥፍጥሬ ጥጥ ተቆልሎ፤*
*ባልሰማ ባላየ በራስ ህሌና እንደበት ታሞ፤*
*ሆድ ሲመች ሲያስተኛ ጨጓራውን አፍግሞ፤*

*በሆነው ባልሆነው በሽታ እንቆቆ ተግቶ፤*
*በለመደው አቆፋዳ በምፅዋት አንግቶ፤*
*በማያልቅ ሀረግ በግጥም ስንኝ ተቋጥሮ፤*
*ጭንቅ ጥብብ ይለው ሲተፋው አንቅሮ፤*

*በዘነበ ዝናብ ባለፈ ክረምት ትዝታ እየጠመቀ፤*
*ዛሬን በምልጃ ሰቀቀን አንግቶ ተስፋ እየሰነቀ፤*
*በቆረረ ፋፋቴ ሳይ መልስ እያስለመለመ፤*
*ሆድኮ ይብሳል ከግንብ ጡብ ካፈለመ፤*

*በነገር ጥይት ሆድ እያረሰረሰ፤*
*በሰይፍ ምላስ ነብስያ እያረሰ፤*
*ብን ብትን ክንፍ ስክር ውልል እያረገ፤*
*እንዴት ይሆን ቀን በህይወት ካረገደ?!*

❖ ♥ ♦



## መንበርተኛ

ህዝብን አቅልሎ ከሸቀጥ እያሳነሰ፤
ባንዳን አብልጦ በደም ዋጅቶ እያበሰ፤
በስልጣን ጥማት ራሱን እያሰከረ፤
ተነስ ግጠም ይሳል ጠሳ እያንቋረረ፤

ደግሞም ሻል ሲለው ሲጠፋው ህልመ ስሲቱ፤
ቅዱስ ካባ ደርቦ ሲሰነስ ማልዶ በንጋት፤
በስሜት በርግጎ ሳይረሳው የራሱ ጥሳ፤
የፀናች መሬት ያናጋል ቀንን ከሲት እያጣሳ፤

የነቃ ቢመስለው ነብስያን ከስጋዋ ግጦ፤
ፀጉር ከቅንድ ብበደማሚት ልጦ፤
ብርሃንን በጣሪያው መጋረጃ ከልሎ፤
አዳኝ ይመስሳል አንጋሎ አንጓሎ፤

ተስገብግቦ በድጥ አፉ በጎመን ሆዱ ሲረታ፤
አይጥ በበላው ዳዋ አስሮ እያስፈታ፤
ዐይኑ ግንባር ሆኖ በመሸታው እያሰደቃ፤
ጭራሮ ይማግዳል ከውሃው እያንቃቃ፤

በመልኮ መንኖ አፍንጫ ሲያስነጥስ፤
ፍሳጎቱ ሲሻው ምኞት ሰማይ ደርሶ ሲመለስ፤
በቅል አቅል መሳት ፈጣሪ ተረስቶ፤
ሲሰመን ቅዱስ ገዳይ ሆነ እርኩሱ ተኝቶ፤



## ድንቄም ምስረታ

*አዳራሹ እንደሁ ከርሞም ጠብቶም የወናፍ፤*
*አንዱ ሲጎለትበት ሀቅን ቀብሮ ከጫፍ፤*
*ሌላው ሲዘንጥበት በሰው የደም ንዋይ፤*
*እረ ወዴት ይሆን ያ የወጋገኑ የማለዳው ፀሐይ?!*

*ድንቄም ተሞሸራ የአህያ ጆሮዎች ካጨበጨቡ፤*
*ትናጎችም ተሰንጥቀው ህሌናን ከሸቀቡ፤*
*ዐይኖችም በክህደት ራስን ከወሸከቱ፤*
*ድሮስ ለምን ይሆን ድንቁን ጥለው ድንቄን ማውሳቱ፡*

*መንደር በነጫጭ የደከረተ ነትብ ጥጥ ተሰልቦ፤*
*ፈርጣማውን ኃያሉን ዋርካ መልጦ በስለት ገልቦ፤*
*ያንዱን ደም ከሌላው አፍሶ ሥጋ እያፋታ፤*
*እህ!! ሰማሁ ልበል ድንቄም ሰው መስርታ፤*



## ✍ ገንዘብ

የሰይጣን ውርስ ተቀብሎ፤
ጌታን በክህደት አቅልሎ፤
አይተው ነገር ራሱን እያጋጠ፤
የገዛ ቅሉን አግንኖ እየሸጠ፤

አንዱን እያነገሰ ሌላውን እያሳጣ፤
በመኖር ምሬት እሬት እያጣጣ፤
በወረቀት ፊት ጣኦትን አትሞት፤
ስንቱን አተልቆ ስንቱን አሳነሰው፤

የስናፍጭ ስጋ አዘልዝሎ እያስበላ፤
በዝናብ ጥብጣብ ወንዝ እያሚላ፤
የራስ ቅል አስጥሎ ሰም እያናፈቀ፤
ጉድ ነውን ልጫን ከግንዱ ያሳቀቀ፤

ሀጥያትን በጫንቃ አሸክሞ፤
በማነኝነት ልብን አሳምሞ፤
የበቆልትን ደም እያስጠጣ፤
ከንቱ ነው ነገሩ በሱ ያስበጣ።



## ሀገሬን እስክሞት አልረሳም

ከነኩሽማ ወገቤን አስረ ምድር እምሳለሁ፡
በአንቀልባዬ አዝዬ ኮኮብ እቀልባለሁ፡
እውነት እውነት እሞታለሁ ሳንቺ፡
ደሜም ይኸው እስኪበቃሽ አንቺ፡

ወስፌ ሆኖ ይውጋኝ የአባቶቼ አጥንት፡
ነፍስ አልባ ያድርገኝ የሰማዩ አባት፡
ከወደድኩሽ ከያዝኩሽ በቅሬ፡
ደብቄ አኖርሻለሁ እኔን አሳልፌ፡

ሳንቺማ ከሆነ ብሞትም እድናለሁ፡
ሰሌኔን አንጥፌ ሳንቺ ስል አልፋለሁ፡
አልረሳም መቼም የቦራዋን ወተት፡
አልሚ ዋርካሽ አሳዳጊ የመናው አለት፡

ሚጢጥዬ እጆችሽ ፍቅርን መጋቢ፡
ፈርጥ ክንዶችሽ ጭንቅን አርጋቢ፡
እንቢ! እንቢ! ለሀገሬ እኔ አለሁ፡
እትሬን ገትሬ ሸቅብ እማሳለሁ፡

ሀገሬን አልረሳም፡
ወገኔን አልክድም፡
አዎ! ሀገሬን አልረሳውም፡
አዎ! ሀገሬንም አልክድም፡



# ✍ እንጃሳ!!!

ቀሽ ቅራቅንቦ - ማገዶ ጎታች፤
ረቡ ረበጥባጣ - ምሳሱ አንጓች፤
ግንድ አልባ - የቢጢቆ ገልቱ፤
ዘንዳስ እንጃ - ወጥቶንስ መገባቱ፤

ደመሳሽ ካባው - በብል ተደፍሮ፤
ጓዳ ጎርጓዳው - በዝንብ ተወሮ፤
እፊያ ጥዶ - አመድ ቢሆን ሽሮ፤
እንጃሳ ጃል - አይሆን መሆኑ አሻሮ፤

ብልጣ ብጥ መሳይ - የኮሶ ነጋዴ፤
ደምሳሽ - የሰው ስም መደዴ፤
ድባብ አጋፋሪ - እባብን አሳባቂ፤
እንጃ ከፍቶ - መኖሩን አስቅሳቂ፤

እጅን ከምንቢሉ - ከገበታው ሆኖ፤
ልብ ከምን ቢሉ - ከምሳር ግኖ፤
ሰው ከምን ቢሉ - ሰጥቶት ካሳ፤
እንጃስ መመለሱ - ቢጎርፍ ጋራሳ፤

መሆንን አንግቦ - መሳልን የተካነ፤
በመፅሐፉ ምሎ - በእምነት የመከነ፤
በዝና ተገዝቶ - በክህደት የደነቆረ፤
እኔ እንጃ - ጀግና ጀግኖ ካቀረቀረ፤

ስሙም ያማረ - ቀልዱ ቅኔ፤
እርስቱ ተራራ - ማንነት ከፈኔ፤
ታሪኩ ዓለም - ጥበቡ የማያልቅ ሜዳ፤
እሱ ነው ወገን - በሀገር የማይወሳዳ፤

*መሬት ተደርምሶ - የዛፍ ባሳ ቢረግፍ፤*
*ሰማይ ዳምኖ - ገሳን ቢያንገፈግፍ፤*
*ወንጭፍ ግሎ - ቢሆን ወንድ ማሰሮ፤*
*መቼም አይመለስ - ማሰው ምሳሩን አስሮ፤*



## ✍ ሰው ፍጡር እንጂ ፈጣሪ አይደለም!!

ዓለም በስሙ  ገና በሱ የኖረች ቢመስለው፤

እሱ በሰጠው ዕየከረሳ ሆኖ ቢታየው፤

እልፍ ባቀፈ ቁጥር ቁና ቁና ቢሸተውም፤

ሰው ፍጡር እንጂ ፈጣሪ አይደለም፤

አሸን ሲበረክት በክረምት አግቢ፤

ዝናብ አረብርቦ አባራው ሲነሳ ከኃያሉ ግቢ፤

በብሌኑ ግንባር በጆሮው ጥጥ ከጠቀጠቀ፤

ሰው አለት እንጂ ነጎድጓድ ባላወቀ፤

ሔሮርስ መቃኑን በሰይፍ ዘልዝሎ፤

ቢበረታ መስሎት የሰጋ ደም በእትሬው አዝሎ፤

በጉልበት በትምክት ሳይኛውን ሸንቁሮ፤

መች ሆነለት ታድያ ሰማይቤት ቆርቁሮ፤



## ✍ ወርቅ

በአፈር ተለውሶ ከምድር ተዋህዶ፤

የበረሐውን ውበት ለጭለማ ማግዶ፤

በዛ የቶን እሳት አካሉን ለብልቦ፤

ወርቅ ራሱ ነው ያማረው ለምልሞ አብቦ፤

በዘነበ ዝናብ መቼም የማይነጥፍ፤

በወጋሪ ቁር ፀሐይ በዝገት የማያልፍ፤

ውርጭ ከአለት የማይበግረው፤

ኃያል ጥበብ ነው ሁሌም የማያልቀው፤

ካነሰ ራስ ታላቅነትን በፀጋው ወርሶ፤

አያልቅበት የወረቃ ውበት ተሳብሶ፤

ሲረታበት ባይለየው ሲያፍም ጭሱ፤

ይኸው ነው የሰው ወርቅ ራሱ፤

❖ ♥ ♦



## ✍ ወርቅ ያዘለ ጀርባ!

የመንደሯ ንጋት በጤዛዋ እሳት ደርቆ፤
ምሳር ሳለ ሀቅ በውሸት ተሰብቆ፤
ከእልፍኟ ባለቤት እንግዳ ቀድሞ፤
ሆድ እያረረ አንጀት ይስቃል ተጋምዶ፤

አድባር እና ቀዬው በሐር ተንቆጥቁጦ፤
ሜዳው ሸንተረሩ በንዋይ ስጥልጦ፤
የምገት አየርሽ ከፅምድረ ገነት ግኖ፤
አመዳይ ይነሳል ገርስሶ ጎርንኖ፤

መዳፎችሽ ስመለም ልበ ደንዳና፤
ያልመነነው ጉልበት ለዋልታው አጣና፤
የአናብስት ውሳጅ ከቋጥኝ የከፋ፤
ታድያ ምን ያደርጋል ወርቅ ከተተፋ፤



# *እስኪ ልጠይቅሽ?!*

አዬ አንቺ ጥንቅሽ መናኛ ዓለም፤

አግማጅ መሳይ ህያው ህመም፤

ዥንጉርጉር ውስጠ አሸን ክታብ፤

እስኪ ልጠይቅሽ? ከፍጡራን ምናብ፤

ያኔ ስዋልል ብውል ከሰው ተራ፤

እንባ አፈስ አፍር ብዬ ብራራ፤

እረ ስምን ጠፋ? ካንዲት ቅጠል፤

እንዲያ ልውል ከቄራው ምልምል፤

ከሰው ተራ አፈር ፈርቶሽ ሳይሆንልሽ ጋሻ፤

ባኒቺ ራሴን ልሰዋ ስድልብ ቀንበር ማረሻ፤

ስዋትት ፈለኩሽ ብጠረኝ እንደ ልጅነቴ፤

ፈራሁ ተብረከረኩ ተሳውሶ መቁ አንጀቴ፤

ወንድሜ የታለህ ጥራኝ ብለህ ጉቼ፤

እህቴም ድገሚው ደስ እንዲለኝ ቡቼ፤

የትፍትፍ እሳት ቶን በዐይኖቼ ሞልቶ፤

ሰንኮፍ ቤቱን ሰራ እውነትሽ ጠፍቶ፤

ይብቃኝ ጥሩኝ  ብሳችሁ ዳቦሌ፤

ሆድ አልችል ቢለኝ ተግቼ ክልሌ፤

ተመልካች አጥቼ ረገፈልሽ ክንዴ፤

እምዬን እያሉ መጥራት ሆኖ ልምዴ፤

ቆይ እስኪ እምን ጋር ልያዝሽ፤
ከምኑስ ደብቄ እንዴትስ ሳኑርሽ፤
እያቸው እጆቼን የገል አፈር አመድ፤
ያልበቃ ቢመስል ታብየው በምስስ ስምድ፤

ዐይኖችሽ አይዙሩ እይታቸው ይድማ፤
ባይሆን ካልታየሽ ልዋጣ ሽቅብ ከማማ፤
ደሞ ደግሞ ይታይሽ ዘመን ሲፈርስ ገልቱ፤
በመኖር ህይወት ሲያልፍ ግልታች ገልቱ ከንቱ፤

ሰንኮፍሽ ሞልቶ ከወስፌ ቢበጣ፤
ደምሽ ጎርፎ ወንዝ መሄጃ ቢያጣ፤
በቀን ሰው ሆኜ አድንሽ ይሆናል፤
ወይን ሳጣሽ እገልሽ ይሆናል፤

ግን እንድረሳሽ ስምን አትተይኝ!
ከዕቶን ፍምሽንስ ስምን አታስጥይኝ፤
ስነገሩማ ብርቅሽ ሰሳምሽ ጥሎኝ ሄዶ፤
መች ሲተወኝ የምጥ ቀን በህልም ማዶ፤

ቆይ ስመሆኑ ስማን ጥስሽኝ ወዴት ሄድሽ?!
ስሞቴስ ቀን ቆርጠሽ ስምንስ አፋረድሽ፤
ዛሬን ደርሰሽ ጣቴን ልታስቆረጥሚ፤
ስምን ይሆን የሆንሺህ ፍርድ ሰሚ?!

አንደበተ ጉልዳም አንገተ እትሬ፤
ስጋ ቢሆን ሸክም ምፅሳደ ጥሬ፤
ምን አይቼ ልፍረድ አጥቼ አባሪ፤
ለእምስ ምልክት ከሆንኩ ነጋሪ፤

ቆይ ግን ከኔስ ምን አጣሽ ምንስ፤
ሆነሽ ትጠይቂኝ የርዕዮት አድማስ፤
በመዳብሽ ወርቅ ከወዲት ታናቢኝ፤
ባልሰጠሽኝ ዘመን እንዴትስ ትከሺኝ፤

ግን ግን ለምን ዋሸሺኝ የስጋዬ አካፋይ፤
ልስማ ትናገሪ እንደሁ እናዳልሆን አባይ፤
ፈርተሽ አታስፈራሪኝ ንገሪኝ በሞቴ፤
አሸን ነን ተንፍሺው እማ ሆይ እቴቴ፤

መኖር እንደ ሀፅያት ቢያምሽ፤
ሞት ቢከብድ እውነት ቢመርሽ፤
ትስማን ይች ደንቆሮ ዓለም፤
ብጉር አድሮ ሳይሆንብን ህማም፤

ስሚ አንቺ የድር መንገድ እሬት፤
የሽክምክም አሽከር የአጥናፍ ባለቤት፤
ከእንግዴማ መጣሁ ሳዘምት ለዘምትብሽ፤
ኡሪ በይ መአበል አብዮት ተከተይ ይለይልን ተነሽ፤

ልይሽማ አንቺ የትንሽ ልት፤
የቅፍቅፍ የእንቅልፍ ጋን ኮተት፤
ወረት አንቅቶ ሊኖር በምድርሽ፤
ሳያሻንም አይቀር የምር ጦርሽ፤

ጥበብ ብታምጥ አሽን ወልዳ፤
መርገምት ቢበዛ በክፉ አዳ፤
ከመልኩ ባይሆናት እድለቢስ የፍጥረት ከንቱ፤
እሷው ናት ማቋሚያው የረገማት ጨርቀ ብዙ፤

ምጥሽ ብዙ ዕምር ክታብ፤
ረገረግ ሀረግ መሳይ ባለ እንብርት፤
አዕምሮሽ ከርታታ ጉድሽ ሰርግ፤
አያበቃ እውቁ የድግስሽ በግ፤

ስጋ አለህ አሉኝ እትብት፤
መግቢያ ክብር የብር ቤት፤
በኩር አልባ የክረምት ሙሽራ፤
ማህፀንሽ ከንቱ ሽንቁር ሻራ፤

የስሜት በር እጀ ጥፍራም፤
ሰውኛ እልቆ ቢስ የትርክ ሰም፤
የባህር ግንባር ጠርዝ፤
ባለ ህብረ ግብር ወንዝ፤

የህፃን ኽርቅ መሳይ ሸንጎ፤
ፍቅረ ዘመድ ውታፍ ፋርጎ፤
የጠሳ ድፍድፍ ምርጊት፤
እርክስና የወራት ምጠት፤

በትዕግስት ተግቶ ሲኖር መጥፎ፤
ከልቡ ተኖ ሲያልቅ የንብ ቀፎ፤
እልፍ ቀን ካልሆነልን መሳ፤
ምንስ ሲበጅ የወይን አንቡሳ፤

በፊቷ ማድያት መታጠብያ በዝቶ፤
አንድ እንኳን የሚያዝንላት ጠፍቶ፤
ዘባች ብቻ ተጠቅጥቆ ከቀዬ መንደሩ፤
ከሥፍራው ቃል ተበጠሰ የእምነት ክሩ፤

ለክፉ ርሃብተኛ ቅምሻ ያጣ፤
ሳያስመኘው ሳገሩ ሰው ባሳንጣ፤
ቀን ቅን ጥሎ ቅል እያዋለለ፤
እልፉ ምስጉን ሲያሻው ዋለ፤

ወሰን ድንበር ያጣ፤
ከልካይ አልባ የበግ ጋጣ፤
መሬት መንታ አሶሳጁ በዝቶ፤
ሞራም አታከተኝ ህልም ፈቺ ጠፍቶ፤

የቅጥር ባለቤት የመዳሪያ አዳራሽ፧
የሰርገኛ ቁዳሽ ብጣሽ ቁራሽ፧
ዛር አንጋሽ ቢያምጥ ከእልፍኜ፧
አልሰጥም ደሜ ና አጥንቴን ሳምኜ፧

በቀለመ ዳር ዘመን ፍች አግቢ፧
ዝል ዛላ በጣሽ የሬት ሞት መጋቢ፧
ከካራው አልቀርም የቀለጠው ስሜ፧
ሞትን አልተወውም ቢያስምጠኝ ከደሜ፧

ባል በሳም ተረግዞ ባልጠጣም፧
ሆዴ እየማቀቀ አፍ ኖሮ ባይርበኝም፧
ይኸው በፍለጋሽ ዛሬን ደርሻለሁ፧
ሳላገኝሽ ማር ሲላስ አፈር እምሳለሁ፧

ምን ያደርጋል ታድያ የሰው ምሳር፧
የጡንጅት ሳር ሸርክትክት አሳር፧
ፈራጅ በሀገሩ አድርጎት ሁሉን ሰው፧
በሉ ተጫወቱት እኔማ ልሄድ ነው፧

በመቅኖዬ ሙሉ ተጫምቶሽ ተራ ጣጣ፧
አድርገሽኝ ያሞሌ ጨው ባጣ ሴጣ፧
በምርቅዝ እግሮቼ እስክጠላሽ ምዬ፧
እስኪ ፈርደሽ እረገሚኝ እምዬ፧

ጤፍ ገብሱ ከማፍሪያው ተሳቆ፤

እስትንፋስ ጎተራው ባሻው ጉሊት ልቆ፤

ስንዴና እንክርዳድ በቅሉ ባንድ ጋይ፤

ባቄሳም ሆድ ብሶት ዋስ ክምር ሳይ፤

አመል ውሃው ግንድ ሆኖ ቢዞረው፤

ሞኝ ብሬ ዶፉን ከቤት ቢያውሰው፤

ምሬት በዝቶ እህል ያስመሬት ቢጋይ፤

ሰሲጡም ቀን ጥሎት ዋስ ከድንጋይ፤

ክፉ አዳጊ ዝርጥ ጉማጅ ልጣጭ፤

ውስ ፈርስ አሳዳጊ መልስ ረጋጭ፤

የመጣያ እሳት የተምች ምች፤

ቂም ቆራሽ ልበ ደም ተንከራታች፤

ያባት ቦንዳ ንቅ ንቆሽ፤

ያዳም እልፍኝ ጡት ንካሽ፤

እጅ አልባ ምፅዋት ዋታች፤

ቆይ እስከመቼ ይኖር በስብ አማች?!

ሳላውቅሽ መዳረሻ ጠፍቶኝ፤

አልፈልግሽ ሆኖ መባቻሽ ታጥቶኝ፤

መድረሻ መወጣጫው በትብታብ ታጉሮ፤

እንዴትስ ይወጣ ሳይለግም ተረከዝ ተቋጥሮ፤

ደርሶ አሳነሳው ነገር ህልም የወደቀ ገሳ፧
ሳልተውሽ አልመለስ ሆኖ ባይሻኝ ምህሳ፧
ይቅርታ ካልፈታው ቂም በቅሉ ካንጀቴ፧
መቼም ሳይመለስ ተቀብሯል እትብቴ፧

ስነገሩ የእንባ ሳቅ ስጋዬን አድርጎት ማገዶ፧
በመርገምት ቻው አልልሽ ነገር መፈጠሬ ገዶ፧
ካንደበት ሳንፃም ህይወት ከአፍ አንሳ፧
ታሳቅ እምነት እንቢ ብሎ በኩዳዴ ተገሳ፧



## ✍ የጭን ቁስ አሜኬሳ

ተዘርቶ ሳይለቀም የሾህ አሜኬሳ፣
ተበትኖ ሳይሰበሰብ የአሸን ሳባ፣
ከበግ ሲሰይፉት ሳይታጣ ጭቁን ስጋ፣
ቀቢፅ ሳይቀርለት ሞት ሰድፎ ብርገጋ፣

ከጭን ቁስል አዝሎ ከራርሞ ምንገሳ፣
እየሩስ ዓሌም ጭንቋን በአና መንድሳ፣
ሩዋንዳም በኢማኪዮሊን መክሊት በኩራ፣
ጥቁሩ አንበሳ ከነጩ አማዞ የካራ አታካራ፣

ከርሞ ከራርሞ ሳይተውን ሽንፋሳ፣
ቢርቁት ሳይርቅ ክፉ የቁም ጥሳ፣
ሰውነት ሳይወጣው ከእንግዴ ልጅ፣
ማስምሶ ማጉረስነው ከዛው ከፅዳጅ፣




# በደም አጥንት የጨቀየ ስጋ

ተንኮልን አርግዞ በቅናት የቆመ፤
በውሃ ተግቶ ራሱን ከደም ባህር ያሰጠመ፤
በአጥንቶች ታጭቶ ከብናኝ የበነነ፤
እፍኝ ነው ከሰውነት ጎዳና ወጥቶ የመከነ፤

ለወጉ ኮርቻ ለአንበሳው ድር፤
ለኖረው ጉልቻ ለሞቱም አድር፤
የንጋት ጎፈር የአድባብ ጭለማ፤
እሱ ነው ያሳጣው ከከልካዩ ማማ፤

ያደም የሌለው የደም ሰንጋ፤
የወበየ ፈርስ ድልብ መንጋ፤
ፈረጠመ ሲሉት ሲሆን እንደ አለንጋ፤
ድሮም ከንቱ ነው በደም የጨቀየ ስጋ፤



# 8ኛው ሺኅ ዘመን

የሄዋኔ አዳም የፍጡፕ መቡከሪያ፧

የእንቁርቁር ውሃ የምንጩ አለም ቋያ፧

የግዛቱ መንበር ያምሳዩ መጋጣ፧

ጊዜ ወር ባመት እየዋጀ ስምንት ሺሕ መጣ፧

ብስሉን ከጥሬው እየቸረቸረ፧

እርጥቡን ከደረቅ እየገረገረ፧

ነፃውን ከድፋን እየቀሳቀሰ፧

መጨረሻው ዘልቋል እየገሳገሰ፧

የድንጋይ ስብ በቅጥቅጥ እንዳሳበረ፧

ስንት ወልዶ ስንት እንዳልዳረ፧

አክናፍ ቅል ስቷት ትኳን ወልዳ፧

ጭሳንጭል ሆነ ስምንተኛው አዳ፧

አፈር በብቃዩ ስምስም እንዳሳጣ፧

ነፋሳትም ከፀሐይ ሳይሆኑ ባሳንጣ፧

ስፍራ መንደራውም እንቆቆ ተግቶ፧

ሳይድን ይባትታል ምድር ሰማይ ወጥቶ፧




# ያወጣት!!

*ገና ባፍሳው ዕድሜ በዛ በለጋው፤*
*ከመንስዔው መንደር ቁል ደጋው፤*
*መሸንተፍ መሰደር በቁሙ ተግቶ፤*
*እውነትም ተሳገች ምክንያት ውሃ ጠብቶ፤*

*ህሌናውን በውሻጥ ወሽጦ፤*
*ራስ ቅሉን በስሜት ጎሽጦ፤*
*ቢሰስጥን መስሎት ሰይጥኖ፤*
*ይጫወት ጀመረ ዘር በዘር በትኖ፤*

*አብዮት አዝምቶ ችግር ሳያወጣ፤*
*ከብረት ተዋድቆ መረቅ ሳያጠጣ፤*
*ከሰንኮፍ ተወልዶ በጥልቁ ሲረታ፤*
*ድንጉሷን ድማም ያወጣት ተመታ፤*



# ✍ አንድ ሴት አየሁ!!

እርር ምርር ያለ እንባ የምታነባ፤
ጭብጥ ኩርምት ያለች ሆድ የምታባባ፤
እንክትክት ጉኝጬቿ ቅስም የሚሰብር፤
አንድ ቋያ ሴት አየሁ ከፍም ግርግር፤

    ደግሞ ፍጥጥ ስል ከመቃኗ ጉያ፤
    አንዳንዴም ሳደምጠው የሆዷን ማባያ፤
    ተስፋዋ በጭንቅ ተሰብሮ ካንባሯ፤
    ብቻ አየሁ ፍም እቶን ከግንባሯ፤

ልጥጥ ሲል መሳ ስስ ሰውነቷ ፤
አጎንብሶ ሲያቀረቅር መለሎ አንገቷ፤
በእጆቹ ዳበሳ ከቅልም መቅለሷ፤
ውክብ ሲል አየሁ የራሰው አቅሷ፤

    ትንፏ*ሿ* እስትንፋስ ቁርጥ ሲለው፤
    ብርክክ ስትል አምጣ ልትወለወደው፤
    በደረቷ ዙፋን ትርታ ነግሶ፤
    ሞት ሲጨፍር አየሁ ቀን ደግሶ፤

ቀና ጎንበስ መለስ ቀለስ፤
ፍር ፍርስ ስትል ፍስስ፤
በህይወቷ ሰይፍ ቃታ ቀጥታ፤
ከበጎኗ እንፉቅቅ አየሁ መዳሂያ አውጥታ፤

በል በቀቀን ቀን አጎንብስ ብሳ፤
ከዛፍ ባሳ ቅጠል መልምሳ፤
ብድግ ስትል ውስጧን አሰባብሳ፤
ከእትሬዋ አየሁ ወኔ ስታነሳ፤

እንጀራ አስፍታ ልትበላ ከድና በወስከንባ፤
አዬ የሷ ነገር ደግሞ ሻል ሲሳት ባሳ ልታገባ፤
ስለትም ከቃንጃው ስሳ ስጋ ልትበሳ፤
አየኋት ብቻ ልጠብስ መስሏት ደም ስታፈሳ፤

ከመባቻ እስከ እልቂት ወልዳ፤
የቡቃያ አገዳ ከእሳቱ ማግዳ፤
እናትነቱንም በፉጨት አምልሳ አማሳ፤
ደግሞ ጅንን ኩርት ጥብርም ያምራታል፤

ትዞር ተዟዙራ ከርሞም እዛው ሳያት፤
ጭንቀቷ አገርሽቶ ሰቀቀን ሲያስገማት፤
መልስ መልሳ ጠያቂው ሲጠፋት፤
ከዛው ታረግዛለች ፍት ፈታ አግብታ፤

ትንታ ሲውጣት ከጓንጉር እንቅርቷ፤
በሽረሪት ድር ሳትድን ልትል ቷ፤
ወርቅ አዝሳ ዓለም ስትዋኝ በምናቧ፤
ትኩር ብዬ አየሁ ሲበጠስ ምሯኗ፤

በእፍኝ ተዘገና ለማያልቅ ወንዝ፤
በዳመናው ድንድን ቅንቅን ሲልበት ወዝ ወዝ፤
ዝናብ ሲያረበርብ እልፍ ጎርፍ ሲጠጣ፤
*አ*ረ ስንቱን አየሁ ምልጥልጥ መሳጣ፤

ከትላንቱ ዛሬ ሳታውቅ ታዝላ ባንቀልባ፤
ሳም ወተቷ ተፍቆ ልጅ ልታሳድግ ደም ታልባ፤
ውሸት ሀቅን ገላ በይቅርታ አንጋላ፤
አየሁ ጉድ ፈርዖንን ከሙሴ አዋልዳ፤

ከባህል ከወጉ ከሁሉም ተጠምቃ፤
በህዳር በታህሳስ ከስጋው ደም ጠልቃ፤
ጥር ላይ መንኩሳ በሰኔ ከማሁ፤
ሳይበቃት አንብታ እጅግ አየሁ፤

❖ ♥ ♦



**በአሻንጉሊት የተሞቡ ሰውነቶች ባለፀግነትን በራሳቸው እጅ የተቀዳጁ ቢመስላቸውም ጤቅ ሞንቅላቶቻቸው ግን ከደረቀ ልክ እንደሚፈረከስ የድንጋዮች ላይ ጧሞች ብቻ ናቸው።።**



## ✍ አንድ ሴት አየሁ!!

*እርር ምርር ያለ እንባ የምታነባ፤*
*ጭብጥ ኩርምት ያለች ሆድ የምታባባ፤*
*እንክትክት ጉንጮቿ ቅስም የሚሰብር፤*
*አንድ ቋያ ሴት አየሁ ከፍም ገርገር፤*
*ደግሞ ፍጥጥ ስል ከመቃኗ ጉያ፤*
*አንዳንዷም ሳደምጠው የሆዷን ማባያ፤*
*ተስፋዋ በጭንቅ ተሰብር ካንባሯ፤*
*ብቻ አየሁ ፍም እቶን ከገንባሯ፤*
*.........................*

*ከውስጣዊ ስሜቷ እስከ ውጫዊ ገፅታዋ ያቺን ሴት በምናቡ እየሳለ ገጣሚው ይመፃደቅባታል፡፡ ብቻ ግን ከእሷ በባሰ እሱ እየባተተ ይመስላል፡፡ ስቃዩዋ በርግጥ መጥፎ ህመም ነው፡፡ ጊዜው ካልዘገየ ሰውነት ካልዛለ መባቻው ግን ፍቅር ቢፅ ከማሁ ብቻ ነው፡፡*

*ገጣሚ፡- አብነት ሲራጅ*